MCPS
ROCKVILLE, MARYLAND

# ለ1ኛ የማርክ መስጫ ክፍለጊዜ የ4ኛ ክፍል የወላጆች መመሪያ

በ1ኛ ማርክ መስጫ ወቅት፣ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክሂሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።
እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በግራጫማ ቀለም/ከለር ክህሎትን እና ጽንሰሃሳቦችን ትምህርት ተሰጥቷል፣ ነገር ግን በሪፖርት ካርዱ ላይ ማርክ አልተጻፈም።

## የሒሳብ ትምህርት

### ቁጥሮችና ግብረቶች በኣስሮሽ ቤት

- ባለ ብዙ-ዲጅት ሙሉ ቁጥር ላይ፣ በአንድ ቦታ ላይ ያለ ዲጅት ከበስተቀኙ ከሚወክለው 10 እጥፍ እንደሚወክል ግንዛቤ ውሰድ/ጂ። ለምሳሌ፣ የቦታ ዋጋን እና የማካፈልን ፅንሰሃሳቦች ኣገልግሎት ላይ በማዋል 700 ÷ 70 = 10 መሆኑን ማወቅ።
- ባለ ኣስር መደብ ሙሉ ቁጥሮች፣ የቁጥር ስሞች፣ እና የተስፋፋ ፎርም በመጠቀም ባለበርካታ-ኣሃዝ ሙሉ ቁጥሮች ማንበብና መፃፍ።
- >፣ =፣ እና < ምስሎች በመጠቀም ሁለት ባለበርካታ-ኣሃዝ ቁጥሮች ማወዳደር።
- ባለብዙ-ዲጅት ሙሉ ቁጥሮችን ለየትኛውም ቦታ ለማጠጋጋት የቦታ-እሴት አጠቃቀም ተረዳ/ጂ።
- በመደበኛ ስልተ ቀመር/algorithm በመጠቀም ባለበርካታ-ኣሃዞች ሙሉ ቁጥሮችን ኣቀላጥፎ መደመርና መቀነስ።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- የማባዛት እኩልነት ምልክትን እንደ ማወዳደሪያ (ለምሳሌ፦ 35 = 5 × 7 ማለት 35 አምስት ጊዜ 7 እንደሚሆን እና ሰባት ጊዜ 5 እንደሚሆን ተርጉም/ሚ።
- ብዜታዊ ማነፃፀሪያዎችን በማካተት በቃላት የሚገለጹ ፕሮብሌሞችን ለማቃለል አባዛ(ዢ) ወይም አካፍል(ይ)።
- ባለ-በርካታ ደረጃ የቃል ፕሮብሌሞች ከሙሉ ቁጥሮች ጋር በኣራት ግብረቶች በመገልገል መፍታት፣ ቀሪዎች መተርጎም ያለባቸውን ፕሮብሌሞች ጨምሮ። ላልታወቀው ብዛት በሚቆምለት ሆሄይ ባላቸው ቀመሮች በመገልገል እነዚህን ፕሮብሌሞች መወከል።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- ኣንድ ፅሁፍ በግልጽ ምን እንደሚል በሚገለፅበት ጊዜ እና ክፅሁፍ ሃሳቦች በሚወሰዱበት ጊዜ በፅሁፉ የሚገኙ ዝርዝሮችና ምሳሌዎችን መጥቀስ።
- ከአንድ ጽሑፍ ዝርዝር ታሪክ ዋነኛ ጭብጥ/መሪ ሃሳቡን ለይ።
- በአንድ ጽሑፍ በተለየ ዝርዝር ላይ በማተኮር ገጸባህሪ፣ መቼት (የመነሻ/የክስተት ቦታ)፣ ወይም የታሪኩን ሁነት፣ በዝርዝር በጥልቀት ግለጽ/ጪ።
- የተለያዩ ታሪኮች የሚተረኩበትን ኣስተያየቶች፣ በመጀመርያ- እና በሶስተኛ-ወገን ትረካዎች ያሉ ልዩነቶችን ጨምሮ፣ ማወዳደርና ማነፃፀር።
- የተመሳሳይ ዘውጎች/ጭብጦች እና ርእሶች (ለምሳሌ፣ የጥሩ እና የመጥፎ ኣንፃራዊነት) ኣያያዝን በታሪኮች ውስጥ ማወዳደርና ማነፃፀር።
- ለ4ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆነን ስነ ፅሁፍ ማንበብና መገንዘብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ ፦ መረጃዊ

- ኣንድ ፅሁፍ በግልጽ ምን እንደሚል በሚገለፅበት ጊዜ እና ክፅሁፍ ሃሳቦች በሚወሰዱበት ጊዜ በፅሁፉ የሚገኙ ዝርዝሮችና ምሳሌዎችን መጥቀስ።
- የኣንድን ፅሁፍ ዋና ሃሳብ መወሰን እና በዝርዝሮች እንዴት እንደሚደገፍ ማብራራት፤ ፅሁፍን ማጠቃለል።
- በአንድ ክውነት ርእስ ላይ ከምንጩ የተገኘ መረጃ/ኢንፎርሜሽን እና ከሌላ በስሚ የተገኘ መረጃ/ኢንፎርሜሽን አወዳድር(ሪ)/አነፃጽር(ሪ)።
- ለ4ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆኑ መረጃያዊ ፅሁፎችን ማንበብ እና መገንዘብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት እውቀት እና አጠቃቀም

- በ4ኛ ክፍል ርእሶች እና ጽሑፎች በርካታ በህብረት የሚካሄዱ ገቢራዊ ውይይቶች ላይ በዉጤታማነት ተሳተፍ(ፊ) (አንድ-ለ-አንድ፣ በቡድን፣ እና በመምህር-የሚመራ)።

## ጽሑፍ

### ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር በውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክዉነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካ መጻፍ።
- ተሞክሮዎችን እና ክውነቶችን ለማዳበር ወይም ለሁኔታዎች የገፀባህርያትን መልሶች ለማሳየት በውይይትና በገለፃ መጠቀም።
- ከተተረኩ ተሞክሮዎች ወይም ክውነቶች የሚከተል ኣንድ መደምደሚያ ማቅረብ።

### መረጃ የሚሰጥ/ትምህርታዊ/ገላጭ

- ርእሱን በግልጽ በማስተዋወቅ ተመሣሣይ/ግንኙነት ያላቸው ሀሳቦችን በአንቀጽ እና በክፍሎች ማጣመር፤ የአቀራረብ/ይዘታን (ለምሳሌ፦ የአርእስት አፃፃፍ)፣ ማሳያ/ለማብራሪያ የሚያገለግል፣ እና መረዳትን ለማገዝ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ ልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎችን ጨምሮ፡፡
- ርእሱን በተጨባጭ ነገር፣ ትርጉሞች፣ በተጨባጭ ሊታዩና ሊዳሰሱ በሚችሉ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ ወይም ከ ርእሱ ጋር የተገናኙ ሌሎች መረጃዎች/ኢንፎርሜሽኖች እና ምሣሌዎች በማዳበር፤ በተወሰነ ክፍል ላይ ያተኮረ መረጃ ወይም በቀረበው አስረጂ ላይ የመደምደሚያ ሃሳብ ስጥ/ጪ።

### ኣስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- አንድን ርእስ ወይም ፅሁፍ በጥራት ማስተዋወቅ፣ አስተያየት መሰንዘር፣ እናም የጸሐፊውን ዓላማ ለመደገፍ የተዛመዱ ሃሳቦች የሚመደቡበት ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- እድገቱና ኣደረጃጀቱ ለተግባር፣ ኣላማ፣ እና ለኣድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮች እና ከጎልማሣ ሰዎች መመሪያና ድጋፍ በማግኘት፣ በእቅድ አዘገጃጀት፣ ክለሳ በማድረግ፣ እና በማረም ፅሑፍ አዳብር(ሪ) እና አጠናክር(ሪ)። ጽሑፍን ለማዘጋጀት እና ለህትመት እንዲሁም ከሌሎች ጋር ለመግባባት እና ለመተባበር፣ በኪቦርድ አጠቃቀም አንድ ጊዜ ተቀምጠህ(ሽ) ቢያንስ አንድ ገጽ ታይፕ በማድረግ በቂ ችሎታዎችን ለማሳየት ኢንተርኔትን ጨምሮ ተክኖሎጂ ተጠቀም(ሚ)።
- የአንድ ርእስን የተለያዩ ገፅታዎች በመመርመር እውቀትን የሚገነቡ ኣጫጭር የምርምር ፕሮጀክቶችን ማከናወን።
- በተራዘመ የጊዜ ገደቦች እና ኣጫጭር የጊዜ ገደቦች ወይም በዲሲፕሊን-በተለዩ ተግባሮች፣ ኣላማዎች፣ እና ታዳሚዎች በዘልምድ መፃፍ።

### የቋንቋ ጥቅም

- በአንድ ርእስ ወይም ጽሑፍ ሪፖርት ማድረግ፣ አንድ ታሪክ መንገር፣ ወይም አንድን ተሞክሮ በተደራጀ መንገድ መተረክ፣ ዋናዋና ሃሳቦችን ወይም ጭብጥ መልእክቶች ለመደገፍ በተገቢ ሃቆች፣ እና አስፈላጊ፣ ገላጭ ዝርዝሮች በመጠቀም፤ ተቀባይነት ባለው ፍጥነት በጥራት መናገር።
- በእፃፃፍ፣ ኣነጋገር፣ በምንባብ፣ ወይም በማዳመጥ በቋንቋ እውቀት እና በህጎቹ መጠቀም።

## ሳይንስ

### የህይወት ሳይንስ

- በእጽዋት፣ በእንስሣት፣ አበስባሽ ንጥረነገሮች፣ እና አካባቢ መካከል የቁሳ አካላዊ ነገር እንቅስቃሴን ለመግለጽ ሞዴል አዘጋጅ(ጂ)።
- እፅዋት ለእድገት የሚያስፈልጓቸውን ቁሳቁሶች የሚያገኟቸው በዋነኛነት ከኣየርና ከውሃ ነው የሚለውን ሙግት መደገፍ።

### ፊዚካል ሳይንስ

- በእንስሳት ምግብ ዉስጥ የሚገኘው ሃይል በኣንድ ወቅት ከፀሃይ እንደነበር ለመግለፅ በሞዴሎች መጠቀም።

### ኢንጂነሪንግ ንድፍ እና ሂደት

- በርካታ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሄዎችን መፍጠርና ማወዳደር።
- ተለዋዋጮች ቁጥጥር የሚደረግባቸው እና የመውደቅ ነጥቦች የኣንድ ሞዴል ወይም የመጀመርያ ናሙና ገጽታዎች ለመለየት የሚታሰቡባቸው ፍትሃዊ ፈተናዎች ፕላን ማድረግና መፈፀም።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ጂኦግራፊ

- ቦታዎች ያሉበትን ለመለየት እና የነዚያን ቦታዎች ሰብኣዊና ፊዚካዊ ጠባዮች ለመግለፅ በጂዮግራፊካዊ መሳርያዎች መገልገል።
- በሜሪላንድ እና በዩናይትድ ስቴትስ የህዝብ እድገትን፣ ፍልሰትን፣ እና የሰፈራ ቅርፀቶችን መግለፅና መተንተን።
- ሰዎች የተፈጥሮ ኣካባቢን ለምንና እንዴት እንደሚለምዱትና እንደሚያሻሽሉት እናም እነዚያ መሻሻሎች እንዴት ተፅእኖ እንደሚያደርጉ ማብራራት።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- የመረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ምንጮችን ያሉበትን ማወቅ፣ መምረጥ፣ እና መገምገም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።
- መገናኛ አውታር ላይ ሰላማዊ ተግባሮችን ተጠቀም/ተጠቀሚ።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብን መፍጠርና መገናኘት

- የተለዩ ውጤቶችን ለማግኘት የስነጥበብን ንጥረነገሮችን በመምረጥና በመጠቀም በድርሰት ውስጥ በታዩ ሰዎች፣ እንስሣት፣ እና ነገሮች መካከል ግንኙነቶችን መወከል።
- በሚታየው ምላሽ ላይ የኪነጥበብ ስራዎችን ለመፍጠር፣ የስነጥበብ ክፍሎች፡- ቀለም/ከለር፣ መስመር፣ ቅርጽ፣ ለስላሳነት/ሻካራነት፣ቅርፅ፣ እሴት፣ እና ቦታ/ሥፍራ፣ እና የተመረጠው ንድፍ/ዲዛይን፡- ደርዝ፣ ድግግሞሹ፣ ንፅፅር፣ አወራረድ/እንቅስቃሴ፣ ማመጣጠን፣ እና በአንድነት/በህብረት ማደራጀት/ማዘጋጀት።

### ስነጥበብ አቀራረብና ዝንባሌ/ምላሽ

- አርቲስቶች አስተያየትንና ወቅታዊ ስሜትን በስነጥበብ የቃላት ዝርዝር በመጠቀም እንዴት እንደሚገናኙ ማወዳደርና መግለፅ።
- የተለያዩ አርቲስቶች ስለ ሰብአዊ ተሞክሮ ሃሳቦቻቸውንና ስሜቶቻቸውን እንዴት እንደሚገልፁ ምርጥ የስነጥበብ ስራዎችን በመተንተን መግለጽ።
- ምርጥ የስነጥበብ ስራዎችን በዘውግ፣ ይዘት፣ ፎርም፣ እና በዘይቤ መመሳሰላቸውንና ልዩነታቸውን ለመወሰን ማወዳደር።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- ሌሎች ተማሪዎች ሲዘምሩ ወይም የንጽጽር ክፍሎችን ሲጫወቱ ባለ ምት እና ሜሎዲያዊ ድግግሞሽ የበዛባቸው/ostinatos በትክክል ማቅረብ።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶችና የአለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከአጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ መዝሙሮችና ዳንሶች መጫወት።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- በሶልፈጅዮ/solfeggio ወይም በተወዳዳሪ ስርአት በመገልገል በትሬብል ስታፍ ቀላል ዜማ ማንበብና መጫወት።

### ለሙዚቃ ምላሽ መስጠት

- በአንድ የሙዚቃ ስታንዛ-ክፍል ላይ ተነፃፃሪና የሚደጋገሙ ሀረጎችን ለይ

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### ጤና-አራማጅ አካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ

- በእርፍት የሚገኝ የልብ ትርታን፣ የልብ ትርታ ኣላማ፣ እና በጣም ከፍተኛ የልብ ትርታን ፍቺ መስጠት።
- አንድን ጡንቻ ጥንካሬ እና የጡንቻ ቻይነት እና የለማጣነት/የተጣጣፊነት ባህርይ በመመርመር አወዳድር(ሪ)።

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- የራስ-በራስ-መገምገም እና ግብረመልስ በመንቀሳቀስ ክሂሎቶች መሻሻል አስፈላጊነታቸውን ማወቅ።
- በእጆችና በእግሮች መያዝና ማስተላለፍ ብቃት ማሳየት።

## የጤና ትምህርት

### የአእምሮና የስሜት ጤንነት

- ውጤታማ የመግባቢያ ክህሎቶችን ማወቅ/መገንዘብ።
- በዉሳኔ አሰጣጥ ሂደት እርምጃዎችን መመርመር።

### ኣልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች እፆች/Alcohol, Tobacco, and Other Drugs (ATOD)

- የኣልኮል መጠቀም አካላዊ ውጤቶችን/ጉዳቶችን መለየትና ማገናዘብ/መመርመር።